# ከማርቆስ ሐሳስ እስከ ዳዌ ዘደዌ-- ከጀግና እስከ አተላ

ድሳይ መስከረም

ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል ሲባል ዘመን አልፏል። ጊዜ ካለፈ ደግሞ የወላጅ ገዳይ የሟቹን ልጅ አሳዳጊ ተብሎ ሊሰየም ይችላል ተብሎም ነበር። ዛሬ በኢሕአፓ ላይ ዘመቻ የከፈቱትን የታሪክ አተላዎች ማንነት ስናይ ለመናገርስ እንዴት ደፈሩ ማለታችን የሚጠበቅ ነው። ያለፈውን ታሪክ የታዘብን ገና ሞተን ሳናልቅ ያሳለፍነውን ታሪክ ሊበርዙና ሊቀይሩ ደፍረው የተነሱትን ስናይ ከመገረም አልፈን ልናጋልጣቸው የዜጋ ግዴታ ይወድቅብናል።

ዳዊ ዘደዌ ያልኩትና ራሱን ዳዊ ኢብራሂም ብሎ የሚጠራው የታሪክ አተላ በሰሞኑ በሌሎች ትዕዛዝ በኢሕአፓ ና በህዝብ ታሪክ ላይ ሲያቀረሽ ለማንበብ ማዳመጥ መገደዳችን በአንድ በኩል ይህን ግለሰብ ክቡር እንግዳ ብለው የሚያስጮሁት የህቡዕ የወያኔ ሎሌዎች ማንነታቸውን ለማወቅ በመቻላችን ጥሩ ስንል በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ግለሰብና ጌቶቹንም ማጋለጡ የማይታለፍ ግዳጅ መሆኑን መረዳት ደግሞ ወቅቱ ነው ያሰኘናል። ዳዊ ኢብራሂም ዛሬ የሰራተኞች ማህበር መሪ ነበርኩ ሊል ቢቃጣም ሀቁ ይነገር ከተባለ ይህ ግለሰብ በቅድሚያ ከኢሕአፓ ከበለሳ ከድቶ ወደ ደርግ ፈርጥጦ፤ከዚያም ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ወያኔ ኢሕአፓን ለማጥፋት ሲል በመሰረተው ፎረም 84 ዋና አባል ሆኖ የተሰለፈ፤ ከዚያም በወያኔ ተመልምሎ የሰራተኞችን ማህበር ይቆጣጠር ዘንድ የማህበሩ መሪ ተብሎ የተመደበ ግለሰብ ነው። እግረ መንገዱን ዛሬ ሊሞት እያጣጣረ ካለው ከዳዊት ዮሐንስና ሌሎች ከሀዲዎች ጋርም የቅርብ ጓደኛ የሆነ ነው።በአጭሩ የለየለት ወያኔ ማለት ነው። ጊዜ አልፎ ዳዊ ደዌ በራሱ የግል ምክንያት/በዚህ ፅሁፍ መዘርዘሩ አላግባብ ይሆናል/ ከወያኔ ልዩነት ሲፈጠር በርግጎ ከሀገር ልውጣ ሲል አውጡኝ ብሎ የተማፀነው ያው የፈረደበትን ኢሕአፓን ነው። ይህን ያስተባበረለት የኢሕአፓ አባልና ጓላም በእነ ዳዌ ማጋለጥ በወያኔ የተገደለው ተስፋዬ ታደሰ ነበር። ዳዊ ኬንያ ሲገባ ያስተናገደውና ያቆየው ኢሕአፓ ነበር። ዳዌ ወደ ሆላንድ ሲሄድም ሁሉንም ያቀነባበረውና በሆላንድም ተቀብሎ ያስተናገደው ያው ኢሕአፓ ነበር። ዳዌ በነተስፋዬ የተሰጠውን የብድር ብዙ ሺ ብር መመለስ ባለመፈለጉ ነፍሱን ያዳነውን ተስፋዬን በወያኔ ሰላይነት ኢሕአፓንም በዚህም በዚያም መክሰስ ጀመረ ። በኢሕአፓ አስተባባሪነት ለሰራተኛ ማህብር የተሰበሰበውንም ብዙ ሺ ዶላር ዳዌ በግሉ በልቶ ማወራረድ ሲሳነው የሰራተኛ ማህበር መሪ የነበሩትን መክሰስና ኢሕአፓንም ደግም መወንጀሩን ተያያዘው። ዝቅጠቱ ቀጥሎ ዳዌ በአምስተርዳም የወያኔ ቅጥረኛ ሆኖ ለወያኔው ተጠሪ ለሙሉጌታ አስመላሽ ሎሌ ሆኖ እስከዛሬ እየሰራ ነው። ደሞዙ እንዲከፈለው ደግሞ በየቀኑ ኢሕአፓን መዘለፍ የግድ ይላል። ለወያኔ ሊያድሩ የሚነሱ ሁሉ አፋቸውን የሚያብሱት በፀረ ኢሕአፓ ልፈፋ መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ይህን የወያኔ አሽከር ነው ተቃዋሚ ብለው ጋብዘው በኢሕአፓ ላይ የሚያስጮሁት?

ዳዌ ከሀዲው ክፈት ተብሎ በከፈተው ዘመቻ ራሱን በሚያስገርም መልክ አጋልጧል። በመሰረቱ ደርግ መሆኑን ከዚያም ለወያኔ ማደሩን በማያወላዳ መንገድ አሳይቷል። አሕአፓን የሚከሰው የደርግን የሰራተኛ አዋጅ ወይም የገርነት አዋጅ የተባለውን በመቃወሙ ነው። ሰራተኛውን በማደራጀቱ ነው። ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ታውጆበት ሳለ ሊከላከል በመሞከሩ ነው። ዳዊ የሰራተኛ ማህበር መሪ ሳይሆን በሰራተኛው ዘንድ የወያኔ ተጠሪ ነበርና ስለ ሰራተኞች ትግል ትክክለኛ ግንዛቤ የለውም። ዘቅጦ ለሕዝብ ጠላቶች አድሯልና የጀግኖችን መስዋዕትነት ማክበሩ ይተናነቀዋል። በመሆኑም የሰራተኛ ማህበር ታጋይ መሪና የኢሕአፓም ጀግና የነበረውን ማርቆስ ሀሳስን ያወግዛል። ማርቆስ በደረግ ተደብድቦና ተቀጥቅጦ ብዙ ስቃይን የተቀበለና ከዚያም በዚሁ የአረመኔዎች ጥርቅም የተገደለ የኢትዮጵያ ወርቅ ልጅ ነበር። ዳዊ ስዩሜ ከበደን ይወነጅላል- ቡከን ደፋርና ቆራጡን ሊያማ ቢነሳ አይፈረድበትም። ስዩሜ ከበደ በመንግስቱም ላይ ሆነ በሌሎች ፀረ ህዝቦች ላይ በተሞከሩና በተወሰዱ እርምጃዎች ሁሉ ተካፍሎ የወቅቱ ሌላ ዳዊ ብጤ ከሀዲ በመንገድ ዓይቶ ሲጠቁምበት ከደርጉ ነፍሰ ገዳዮች ጋር መሀል ፒያዛ ተታኩሶ የተሰዋ ጀግና ነበር። ታዲያ እነዚህን ጀግኖች ለመስደብ ዳዊ መነሳቱ ምንኛ ፀረ ህዝብና የጠላት ሎሌ መሆኑን አያሳይም? ዳዊና ኢሕአፓ፤ዳዊና ሕዝብ በተለያየ ጎራ መሆናቸውን የዳዊ ፅሁፍ/ ያውም የእሱ ከሆነ!/ ግልፅ ያደርጋል። ይባስ ብሎ በወያኔ አፋኞች ከቤቱ ሲወጣ የተገደለውን ተስፋዬ ታደሰን ኢሕአፓ ገደለው አስገደለው ብሎ በጠራራ ፀሀይ ይዋሻል፤ ቀጣሪውን ከወንጀሉ ነፃ ለማድረግ ይሞክራል። ዳዊ ደዌ ባለቤቱን እየደበደበ ስትፈታው፤ ወጣቶችን ሊደፍር እየሞከረ ሲከሽፍበትና ስሙ ሲጠፋ ፤ በሆላንድ ያለው ህብረተ ሰብ ሲንቀውና አንቅሮ ሲተፋው ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ የሚያደርገው ኢሕአፓን ነው። ቅዠት ልንለው እንችላለን። በሰራተኛ ማህበር አመራር አባል ሆነው የተሰደዱትንም የሚከሰው የራሱን ጥፋት ለመሸፈን መሆኑ ግልፅ ነው /የሚመለከታቸውም የበኩላቸውን ማለት ይጠበቅባቸዋል በነገራችን ላይ/።ይህ ዳዌ ሙሉ በሙሉ ለወያኔ ያደረ በመሆኑና ውሎ አድሮ ተመልሶም በወያኔ የደፋ ቅጥረኛነት አንድ ውዳቂ ቦታ ሊያገኝ የሚችል ነውና ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻውን የከፈቱት ክፍሎች ቢጠቀሙበት የሚያስገርም አይደለም።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዳዊ ደዌ ግን ጀሌ ነው። ያውም የተሰጠውን ስራ በሚገባ ማከናውን አቅቶት ቡትቶ አቅዋሞችን አስተጋብቶ ራሱንም ቀጣሪዎቹንም የሚያጋልጥ። ዋና ትኩረታችን መሆን ያለበት ባዘዙት ላይ ነው። ወደነዚህ ከመሄዳችን በፊት ግን በአሁኑ ጊዜ በተቀነባባረ መልክ የቅጥረኛ መንጋው ሁሉ በኢሕአፓ ላይ ለምን ሊረባረብ ተነሳ? ዳዊ እንዳለቀሰው ኢሕአፓ ሰራተኛውን፤ወጣቱንና ሴቶችን ሊያደራጅ ከተነሳ /ለምሆኑ ይህ ስራው አይደለምን?/ ከወያኔ ባሻገር ፀረ ወያኔ ነን የሚሉት ለምን ኡኡታ ማሰማት ተገደዱ? ጠፋ፤የለም፤ በሀገር ቤት ዳብዛውም የለ የተባለው ኢሕአፓ ከመ ቅፅበት አስጊ ሆነ እንዴ? ወዘተ ... ዘመቻው በቅድሚያ የተጠየቀው በወያኔ ነው። ይህን የወያኔ ጥሪ በመቀበል ይሁን በራሳቸው ደግሞ ይህን ዘመቻ እያፋፋሙ ያሉት እነ አንዳርጋቸው ፅጌና መሰሎቹ መሆናቸው በአሁኑ ጊዜ የሚደበቅ አይደለም። ከደዌ እስከ ከረንት አፌይርስ ፓልቶክ የኢሰፓ ወያኔ ጥምረት በፀረ ኢሕአፓነት እየታየ ራሱን ለትዝብት እየዳረገ ነው። ፓልቶኩ ወያኔን ረስቶ ኢሕአፓን በዋና ጠላትነት መድቦ ሲጮህ ያነጋል። በዘመቻው ተካፋይ የሆኑትን ደዌ ብጤ ጀሌዎችን በእንግዳነት ጋብዞ ያስጮኻል። ፓልቶኩን መሪ የስንት ወጣት ደም ያፈሰሰች የቀይ ሽብር ኮከብ ገዳይ ሰትሆን በጉሬቷ የሚያጅቧት ሌሎችም ብዙ ነፍስ ያጠፉ ወንጀለኞች ናቸው። (ስማቸው ደግሞ ወደፊት ከነስራቸው ይጋለጣል)። ወንጀላቸው ከሚያስጮኻቸው ጋር ደግሞ የወያኔ ሰርጎ ገቦች ደብለቅ ብለው ዘመቻውን ያጧጥፋሉ። አንዳርጋቸው ፅጌ ዳላስ ሳለ በኢሕአፓ ላይ ዝመቱ ብሎ ማዘዣ ሲሰጥ ያቀረበው ምክንያት ቅንጅትን የሚበጠብጠው ኢሕአፓ ነው የሚል ቢሆንም ይህ ግለሰብ ይህን ዘመቻ የጠራበት ምክንያት ሌላ መሆኑን ማንም አይስተውም። አንዳርጋቸው ፅጌ ለወያኔ የሰራና አሁንም ለወያኔ አይሰራም ብሎ ማንም አፉን ሞልቶ ሊናገርለት የማይችል ግን በጥባጭ ግለሰብ ለመሆኑ ብዙዎች የሚያውቁትና በተለይም በለንደን ስራውን የታዘቡት መስክረዋል። ዛሬ ይህ ግለሰብና በቅርቡ ወደ አሜሪካ የመጣው አለቃውና ጓደኛው የተነሱበት ዋና አላማ የአሜሪካው አምባሳደር ያማሞቶ እንዳለው ተቃዋሚ ሀይሎችን በለዘብተኛ ስም አለስልሶ ለወያኔ ማቅረብና ፅንፈኛ የተባሉትን እነ ኢሕአፓን በዘመቻ ከህዝብ መነጠል ነው።

የተተለመው ተንኮል ምንድነው? የወያኔ አገዛዝ ወደ ከርሰ መቃብሩ እየተጓዘ ነውና መዳኛ ይፈልጋል። ያማሞቶ እንዳለው ደግሞ ወያኔ ከስልጣን መውገዱን አሜሪካ አትፈልግም። ቀውስ ሲባባስ ወያኔ ሊያኀብድዱ ከሚፈልጉ ጋር መጠጋጋት ደግሞ ልምዱ ነው። በ 97ኡ ምርጫ ጊዜ ወያኔ ጨንቆት በነበረበት መልሰ ዜናዊ በድብቅ ኖርዌይ ሄዶ ከኦነግ መሪዎች ጋር መገናኘቱን መለስ ራሱ አምኗል። የኦነግ መሪዎችም በምርጫ አትሳተፍ ያሉት ህዝብ ዘግቷቸው ቅንጅትን፤ኦብኮን ወዘተ በመምረጡ ተደናግጠውና በተለመደው የጠበበ ዕይታቸው አማራው አንሰራራ ብለው ደምድምው ከመለስ ጋር ደግም ሊተቃቀፉ ሞክረው ነበር። አልሰራም። ዛሬ ደግሞ ወያኔ ለዘብተኛ የተባሉትንና ኦነግንም ጭምር ማሰባሰብ ይፈልጋል። ለዘብተኞች ማለት እንደነ አንዳርጋቸው ፅጌ ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ፤ ከወያኔ ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ እንደራደር እንታረቅ የሚሉት ናቸው። እነዚህን ሁሉ ለማስተባበር በሚል (አንጋፋ የቅንጅት መሪዎች ወደ አሜሪካ ቪዛ ሲከለከሉ ) ብርሃኑ ነጋ ግን አሜሪካ ገብቷል። እንዴት ሆነ ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ብርሃኑ ግሪን ካርድ ስላለው ነው የሚል ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው ብርሃኑ ነጋ እስከ 97 ምርጫ ሰሞን የአሜሪካ ዜጋ ነበር። በምርጫው ለመሳተፍ ሲል ግን ኢትዮጵያዊ ዜግነትን ወስዶ ባለ ግሪን ካርድ ሆኗል። ታዲያ ይህ ግሪን ካርድ በየ 11 ወሩ ሰውየው ራሱ አሜሪካ ተገኝቶ ማሳደስ አለበት እየተባለ በቃሊቲ ለብርሃኑ ማን አደሰለት? ነገሩ ግልፅ ነው። ብርሃኑ ነጋ ቅድሚያ ተሰጥቶት ስራውን እንዲሰራና አሜሪካ ላቀደው ከአንዳርጋቸውና ሌሎች ጋር ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ነው። የዚህ ሀቅነቱ ደግሞ ሳይውል ሳያድር የሚታይ ነው። ዕድሜ ይስጠን ብቻ!

ታዲያ ለምን በኢሕአፓ ላይ መዝመቱ አስፈለገ ? ለምን በዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት ላይ ዘመቻው ተቀነባበረ ? በአቶ ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቅንጅት ክፍልስ በጠላትነት ተፈርጇል ወይ? አክራሪ አማሮች የሚለውልፈፋስ ለምን ዛሬ ነፍስ ዘራ? የአንዳርጋቸው ሎሌዎች በደፈናው ዶክተር ታዬን ኢሕአፓ ብለው መወንጀሉን መርጠዋል።ይህ ክስ መሰረተ ቢስ ለመሆኑ ብዙም ክርክር አያሻውም። ዶክተር ታዬ ደግሞ እንደ ማንኛውም ዜጋ በፖለቲካ ድርጅት ገብቶ መስራትን የመምረጥ መብት አለው።በዚህ ላይ ለምን እንደሚጮህ የሚገባ አይደለም። በዶክተር ታዬ ላይ የሰም ማጥፋት ዘመቻ የከፈተው ገሞራው ካሳ ደግሞ የልደቱ ኢዴፓ ሎሌና የዳዊም የቅርብ ጓደኛ መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው። በዶክተር ታዬ ላይ ዘመቻው የተከፈተው በእነ አንዳርጋቸው የተጠነሰሰውን ለወያኔ እጅ እንስጥ፤ ከወያኔ ጋር እንደራደር እንስራ ሴራ ዶክተሩ የሚቃወምና ለማክሸፍም የሚታገል በመሆኑ ነው። የእነ አንዳርጋቸው ቡድን ከወያኔና ከአሜሪካ ጋር ያለውን ትስስር ደግሞ ካየነው ዓመታት አልፈዋልና አንሞኝላቸውም። በዚሁ መሰረት ለወያኔ እጅ እንስጥ ጥሪን በመቃወም ደግሞ ኢሕአፓ ግንባር ቀደም በመሆኑ ኢሕአፓን ማጥቃቱ በወያኔም፤ በከሀዲዎቹም፤በጌታቸውም የሚፈለግ ነው። ምስኪኑ ሰለሞን ተካልኝ ሳይቀር ሊያነብ የተሰጠው ወረቀት ኢሕአፓን የሚያወግዝ ነበር። ትግሉን ለወያኔ አናስረክብም ባዮችን በአክራሪነት ፈርጆ ለማጥቃት የተከፈተውን ዘመቻ የትላንት ደም አፍሳሾች በየፓልቶኩ ማጀባቸው ደግሞ የሚያስገርም አይደለም። ለነገሩ ከረንት አፌይርስ የተባለው ፓልቶክ አንዳርጋቸው ይታዘዝ እንጂ በውስጡ የተሰገሰጉት ቀይ ሽብር አራማጆችና ወያኔዎች የየራሳቸው ግብ እንዳላቸው ግልፅ ነው። ኢሕአፓ ላይ የግልፅም የድብቅም ደባዎች እየተፈፀሙበት መሆኑ ይታያል። ድርጅቱን መንከባከብ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ዶክተር ታዬንም መንከባከብ የሚያስፈልገው ለዚህ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ነው። ወያኔና ባዕዳን የጠነሰሱትን ትግል አፍራሽ ሴራም ማጋለጥና ውድቅ ማድረግ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው።

የእነ ወያኔ ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻ በመሰረቱ ፀረ ኢትዮጵያ ርብርቦሽ ነው። ወያኔ እንዳይወድቅ ጊዜ ለመስጠት የሚደረግ ጥረት ነው። ኢሕአፓ ለዚህ ጥረት እንቅፋት በመሆኑ ነው እየተጠቃ ያለው። በታሪክ የታየ የተደጋገመ ክስተት ነው። ኢሕአፓ ለወያኔ እጁን አይሰጥም። ሊከዱ የተነሱትን ሆነ ያቋመጡትን ሁሉ አጋልጦ ይታገላል። የተከፋፈሉ ድርጅቶች መፈረካከሳቸው ሆነ መዳከማቸው በኢሕአፓ ምክንያት አይደለም። ኢሕአፓ ከህብረት ጋር ሆኖ ኤኤፍዲ የተባለውን አጓጉል ስብስብ አልቀበልም አልደግፍም ማለቱም የሚያኮራና እሰየው ያልነው ነው። ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ ወይም ከወያኔ እንደራደር የሚሉ አቅዋሞች ትግልን ይጎዳሉ፤ ለህዝብ አይጠቅሙም ብሎ መቆሙም የሚያስመሰግነው ነው። ከዳዊ እስከ ወዲ ፅጌና ሌሎችንም ጨምሮ የተከፈተው -ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻ መክሸፉ የማይቀር ነው። ወያኔን ማቀፍ ሳይሆን መጣል ማስወገድ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት። ወያኔን ማቀፍ ግን የባዕድና የቅጥረኞች ተልዕኮ ነው። የኢሕአፓ አቅዋም የኢትዮጵያ ሕዝብ አቅዋም ነውና ኢሕአፓ ለኢምንቶች ጫጫታ የሚበገር አይደለም። ከታሪክ ተማሩ ይላል።

ሁሉም ዜጋ ነቅቶ ትግላችንን ሊያጠፉ የተነሱትን ይቃወም!!!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com